# የኢትዮጵያ የምግብ፣የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ
# አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን

## በባለስልጣኑ ስር ለሚገኙ የቴክኒክ ኮሚቴዎች የአበል ክፍያ
## አፈጻጸም መመሪያ 377/2013

ህዳር 2009

አዲስ አበባ

## ማውጫ

መግቢያ…………………………………………………………………………..1-2

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ…………………………………………………………………3

2. ትርጓሜ………………………………………………………………………..3

3. የተፈፃሚነት ወሰን…………………………………………………………..4

4. የዚህ መመሪያ አላማዎች……………………………………………………4

### ክፍል ሁለት

### የኮሚቴዎች ሃላፊነትና ተግባር እና የስብሰባ ጊዜ

5 .የጤና ሙያ ስነ-ምግባር ኮሚቴ ሃላፊነትና ተግባር………..............................4-5

6. ብሄራዊ የመድሃኒት አማካሪ ኮሚቴ ሃላፊነትና ተግባር....................................5

7. ብሄራዊ የጸረ ተህዋሳያን መድሃኒቶች አማካሪ ኮሚቴ ሃላፊነትና ተግባር…………6

8. የትምባሆ ቁጥጥር ትግበራ አሰተባባሪ ኮሚቴ ሃላፊነትና ተግባር. .....................6-7

9.የጤና ባለሙያዎች የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ኮሚቴ……………………........7-8

10.የኮሚቴዎች የስብሰባ ጊዜ……………………………………………........................8

### ክፍል ሦስት

### የኮሚቴ አባላት ክፍያ አተገባበር

11.የኮሚቴ አባላት ክፍያ………………………………………………………8-9

12.የክፍያ መግለጫ……………………………………………………………9

13.የኮሚቴ አባላት ክፍያ መጠን……………………..........................................10

14.ተፈጻሚነት የሌላቸው ህጎች…………………………...................................10

15. የተሻረ ህግ……………………………………………………………………12

15. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ…………………………………………………12

# መግቢያ

ለጸረ ተህዋሲያን መድሃኒቶች አማካሪ ኮሚቴ የጸረ ተህዋሲያንን መላመድ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ስራዎችን በተመለከተ ለባለስልጣኑ ስለሚሰጠው የቴክኒክ ምክር አበል መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የትምባሆ ቁጥጥር ትግበራ አሰተባባሪ ኮሚቴ አለም አቀፍ የትንባሆ ስምምነትን ሁለንተናዊ ባለው ሁኔታ በአገራችን እንዲተገበር ስትራተጂክ እቅድ በማውጣትና ለዚሁም ግብዓት በማፈላለግ፤ ከሚመለከታቸው የዘርፍ አጋር ድርጅቶችና ህብረተብ ጋር ተግባራዊ እንዲሆን ለማስተዋወቅና የክትትል ስራ እንዲኖር ለማስቻል በሚሰሩ ስራዎች ላይ ኮሚቴው ለሚሰጠው የቴክኒክ ምክር አበል መመወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ብሄራዊ የመድሃኒት አማካሪ ኮሚቴ የቅድመና የድኅረ ገበያ የመድኃኒት ደህንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት ግምገማና ምዝገባ በማድረግ የመድኃኒት ደህንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት በማረጋገጥ አግባባዊ የመድኃኒት አጠቃቀም እንዲኖር ባለስልጣኑ ሃላፊነቱን በብቃት ለመወጣት በሚያስችሉ ስራዎች ላይ ለሚሰጠው የቴክኒክ ምክር አበል መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የጤና ሙያ ስነ-ምግባር ኮሚቴ የጤና ባለሙያዎች ሙያዊና ስነምግባራዊ ብቃት ላይ የሚታይ የስነ-ምግባርም ሆነ የሙያ ብቃት ማነስ ጋር ተያይዞ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በመቀበልና በመርመር የውሳኔ ሀሳብ ለባለስልጣኑ በማቅረብ ለሚሰጠው የቴክኒክ ምክር አበል መወሰን በማስፈለጉ፤

ሁሉም የጤና ባለሙያዎችን ያካተተ የአፈፃፀም ማኑዋሎችን በማዘጋጀትና ባለሙያዎቹ እንደየሞያቸው ተከታታይ የሆነ የሙያ ማጎልበቻ ስልጠና እንዲወስዱ በማድረግ የሚጠበቅባቸውን የሙያ ሃላፊነት እንዲወጡ ለማስቻል የጤና ባለሙያዎች የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ኮሚቴ ለሚሰጠው የቴክኒክ ምክር አበል መወሰን  በማስፈለጉ፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ ስራዎችን ለመስራት ለተመሳሳይ አላማ ለሚቋቋሙ ኮሚቴዎች ለአባላቶቹ የመንግስትን መመሪያና ደንብ ባገናዘበ መልኩ የአበል ክፍያ መወሰንና መፈጸም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፡፡

የኢትዮጵያ የምግብ የመድኃኒት እና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 661/2002 አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 3 እና በደንብ ቁጥር 299/2006 አንቀጽ 98 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

## *1. አጭር ርዕስ*

*ይህ መመሪያ በባለስልጣኑ ስር ለሚገኙ የቴክኒክ ኮሚቴዎች የአበል ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር* **377/203** *ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡*

## 2. *ትርጓሜ*

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ፡-

2) “ኮሚቴዎች” ማለት በባለስልጣኑ ስር የሚገኙ የቴክኒክ ምክር ለመስጠት ተብለው የሚቋቋሙ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ሲሆኑ፤ የጤና ሙያ የስነ-ምግባር ኮሚቴ፣ ብሄራዊ የመድሃኒት አማካሪ ኮሚቴ፣ ብሄራዊ የጸረ ተህዋሳያን መድሃኒቶች አማካሪ ኮሚቴ፣ የጤና ባለሙያዎች የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ኮሚቴ እና የትምባሆ ቁጥጥር ትግባራ አሰተባባሪ ኮሚቴዎችን ይጨምራል፡፡

3) “ባለስልጣን” ማለት የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፡፡

4) “ተወካዮች” ማለት አግባብነት ካላቸው ተቋማት የተወጣጡ ባለሙያዎች ሆነው በኮሚቴ አባልነት ለባለስልጣኑ የቴክኒክ ምክር አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎች ናቸው፤

5) “አበል” ማለት በተለያዩ ኮሚቴዎች ውስጥ የኮሚቴ አባል ሆነው በሙያቸው የቴክኒክ ምክር አገልግሎት ለባለስልጣኑ ለሚሰጡ ባለሙያዎች የሚከፈል የአበል ክፍያ ነው፤

6) “ሚኒስትር” ማለት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሚኒስትር ነው፡፡

7) “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

8) ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ የጤና ሙያ ስነ-ምግባር ኮሚቴ፣ ብሄራዊ የመድሃኒት አማካሪ ኮሚቴ፣ ብሄራዊ የጸረ ተህዋሲያን መድሃኒቶች አማካሪ ኮሚቴ፣ የጤና ባለሙያዎች የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ኮሚቴ፣ የትምባሆ ቁጥጥር ትግበራ አስተባባሪ ኮሚቴ እና ሌሎች ለተመሳሳይ አላማ በሚቋቋሙ አበል ለሚከፈላቸው ኮሚቴዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 4. ዓላማ

በተለያዩ ኮሚቴዎች ውስጥ በአባልነት የሚሰሩ ተወካዮች ስራቸውን በሚሰሩበት ጊዜ በሙያቸው ለሚያበረከቱት የቴክኒክ ምክር አስተዋፅኦ የአበል ክፍያ ሥርዓት እንዲኖር ለማድረግ ነው፡፡

# ክፍል ሁለት

# የኮሚቴዎች ተግባር ሃላፊነት እና የስብሰባ ጊዜ

## 5. የጤና ሙያ ስነ-ምግባር ኮሚቴ ተግባርና ሃላፊነት

1) በጤና አገልግሎት ጥራት ጉድለት እና በባለሙያዎች ሙያዊና ስነ-ምግባርዊ ብቃት ማነስ ምክንያት የሚደርሱ ጉዳቶችን አስመልክቶ በተጠቃሚዎች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ይቀበላል፣ይመረምራል፣መንስኤዎቻቸውን አጣርቶ በውጤቱ መሰረት ለባለስልጣኑ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤
2) አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከባለስልጣኑ ጋር በመመካከር ነጻ የሆነ አጣሪ ወይም መርማሪ በመመደብ የቀረበው ቅሬታ እንዲጣራ ያደርጋል፡፡
3) ተዘውትረው በጤና አገልግሎት ጥራት እና በባለሙያዎች ሙያዊና ስነ-ምግባርዊ ብቃትና ጉድለት የሚቀርቡ ቅሬታዎች ስርወ ምክንያቶች ይለያል፤ እነዚህን

ችግሮች ዘላቂ በሆነ መንገድ ለመፍታት እንዲቻል የፖሊሲ ሀሳቦችን ያመነጫል ለባለስልጣኑ ያቀርባል፡፡

4) በቀረበለት ቅሬታ ላይ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ የሙያ ስራ ፍቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲታገድ ለባለስልጣኑ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡ የቀረበለትን ቅሬታ ለማየት በቂ ማስረጃ መኖሩን ሲያረጋግጥ ቅሬታ የቀረበበት የጤና ባለሙያ ወይም ተቋም መልሱን በሰላሳ ቀን ውስጥ እንዲያቀርብ መጥሪያ ይልክለታል፡፡
5) ሌሎች በባለስልጣኑ በሚሰጠውን አቅጣጫ መሰረት የጤና ባለሙያዎች ሙያዊ፣ ስነ ምግባራዊ እና የጤና ተቋማት የአገልግሎት ጥራት ብቃትን ለማሳደግ የሚያስችሉ ተግባራት ያከናውናል፡፡

## 6. ብሄራዊ የመድኃኒት አማካሪ ኮሚቴ ሃላፊነትና ተግባር

1) የአገሪቱን የጤና ችግሮች ለመከላከልና በሽታዎችን ለመፈወስ የሚያገለግሉ የመድሃኒቶች ደኅንነትና ፈዋሽነት ጥራትን ለማረገገጥ ፣ የተለያዩ ጤና ተቋማትን የአጠቃቀም ደረጃ መመደብ፣ የመድሃኒት ፎርሙላሪዎችና የአንድ ወጥ የህክምና አሰጣጥ መመሪያ ዝግጅትን በተመለከተ ባለስልጣኑ ያማክራል፣
2) በመድኃኒትና በህክምና ዘርፍ በሚገኙ ወቅታዊ መረጃ ላይ በመመሰረት የአገሪቱ የመድሃኒቶች የምዳባ ለውጥ የሚያስፈልጋቸውን በመለየት ለባለስልጣኑ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፣
3) የህክምና ሙከራ ክትትልና ቁጥጥርን በብቃት ለመወጣት የህክምና ሙከራ ሂደትና የአሰራር ስርአት እንዲዚሁም የህክምና ሙከራ ጥናቶች ውጤት አስመልክቶ ለባለስልጣኑ ቴክኒካዊና ሙያዊ ምክር ይሰጣል፣
4) ለህብረተሰቡና ለጤና ባለሙያዎች የመድኃኒት መረጃዎች ስርጭት አስመልክቶ የሙያ ምክር ይሰጣል፡፡
5) የድህንነት፣ የፈዋሽነትና የጥራት ችግር ያለባቸው መድሃኒቶች ላይ መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች የውሳኔ ሃሳብ ለባለስልጣኑ ያቀርባል፣ ሌሎች ከመድሃኒት ደህንነት፣ ፍቱንነት፣ ጥራት እና አግባባዊ አጠቀቃም ጋር ተዛማጅ ጉዳዮችን በተመለከተ ባለሥልጣኑን ያማክራሉ፣

6) በአመት ሁለት ጊዜ ስለተከናወኑ ተግባራት ለባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ሪፖርት ያቀርባል፤

7) ሌሎች ከመድሃኒት ጋር በተያያዘ ባለስልጣኑ የቴክኒክ ምክር ሲጠይቅ ይሰጣል፡፡

## 7. ብሄራዊ የጸረ ተህዋሲያን መድሃኒቶች አማካሪ ኮሚቴ ሃላፊነትና ተግባር

1) በአገራችን የጸረ ተህዋሲያን መድሃኒቶች መላመድን በመከላከልና በመቆጣጠር የሚያገጥሙ ክፍተቶችና መልካም አጋጣሚዎችን በመለየት፤ እነዚህን ችግሮች የሚፈቱበትንና መልካም አጋጣሚዎች የሚጎለብቱበትን ስትራተጂዎች በመለየት ተግባራዊ እንዲሆኑ ያግዛል፤

2) የጸረ ተህዋሲያን መላመድን መከላከልና መቆጣጣር እንዲቻል የተለያዩ ወቅታዊ ፕሮጀክቶችን በማዘጋጀት ያግዛል፤

3) የጸረ ተህዋሲያን መድሃኒቶች መላመድ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የስልጠና ፍላጎት ይለያል፤ የተለያዩ የማስልጠኛ ማተሪያሎች በማዘጋጀት ስልጠናዎችን በማስተበበርና በመስጠት ቴክኒካዊ እግዛ ያደርጋል፤

4) በጸረ ተህዋሲያን መድሃኒቶች መላመድና ተዛማጅ ጉዳዬች ላይ የምርመርና ስርጸት ሳይንሳዊ መረጃዎችን በማሰባሰብ ያግዛል፣ የተለያዩ ተሞክሮዎችን እያየ መረጃ ይይዛል፤

5) በጸረ ተዋህሲያን መከላከልና መቆጣጠር አገር አቀፍ ኮንፈረንሶችና የመረጃ ስርጭት ዝግጅቶችን ያስተባበራል፤

6) የኮሚቴውን የስራ አፈጻጸም ሪፖርት በየሩብ አመቱ ያቀርባል፡፡

## 8. የትምባሆ ቁጥጥር ትግበራ አሰተባባሪ ኮሚቴ ሃላፊነትና ተግባር

1) የትምባሆ አለም አቀፍ ስምምነት አጋር ድርጅቶችን ይለያል ትብብር ያጠናክራል የትንባሆ ቁጥጥር ፕሮግራም ሁለንተናዊና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ መተግበሩን ያረጋግጣል፤

2) የትንባሆ ቁጥጥር ስትራተጂክ እቅድ ያዘጋጃል፤ ለዚሁም ትግባራ የቴክኒክና የፋይናንስ ግብአት ያፈላልጋል፤

3) አጋር ድርጅቶችን የትንባሆ ቁጥጥር ትግበራ፤ ግብአት አቅርቦትና የግንዛቤ የማሳድግ ተግባራት ያከናውናል፤

4) በክልሎችና በከተማ መስተዳደሮች የትንባሆ ቁጥጥር ተግባራት አስተባባሪ ኮሚቴ እንዲቋቋም ያበረታታል ይደግፋል፤

5) ለትንባሆ የቁጥጥር አሰራር መመሪያዎች ዝግጅት የበኩሉ አስተዋጽኦ ያደርጋል፤ ለአጋር ድርጅቶች ያስተዋወቃል መተግበራቸውን ይከታተላል፤

6) የትንባሆ ቁጥጥርን አስመልከቶ በመገናኛ ብዙኃን የማስታዋወቅ ዘመቻ እንዲካሄድ ያግዛል፤ ሂደቱንም ይከታተላል፤

7) የትንባሆ ቁጥጥር አሰመልክቶ የሚዘጋጁ የማሰተዋወቅ ስራዎችን ያስተባብራል፤

8) የትንባሆ የቁጥጥር ስራ በመረጃ የተደገፈ ለማደረግ ምርምሮችና ጥናቶች በተጠናከረ ሁኔታ እንዲካሄዱና በቁጥጥር ሒደት የሚመዘገቡ መልካም ተሞክሮዎች ተለይተው በመረጃ እንዲያዙና መልካም ተሞከሮዎች እንዲስፋፉ ያግዛል፤

9) አለም አቀፍ የትንባሆ ቁጥጥር ስምምነት ትግባራ የክትትል፣ የምዘናና የግምገማ ስርአት እንዲዘረጋና ተግባራዊ እንዲሆን አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

10) የኮሚቴውን የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት በየ6/ ስድስት/ ወሩ ያቀርባል፡፡

## 9. የጤና ባለሙያዎች ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ኮሚቴ ሃላፊነትና ተግባር

1) ሁሉንም የጤና ባለሙያዎች ባካተተ መልኩ የአፈፃፀም መመሪዎችንና ማኑዋሎችን ማዘጋጀት

2) ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ስልጠና የሚሰጡ ተቋማትን መምረጥና እውቅና መስጠት

3) የተከታታይ የሙ.ያ ማጎልበቻ ኮርሶችን እውቅና የሚሰጡ አዲስ ተቋማትን መምረጥና በየአምስት አመቱ ማደስ

4) የተከታታይ የሙ.ያ ማጎልበቻ ኮርሶችን እውቅና የሚሰጡ ተቋማትን ቅድመ እውቅና የሰጡአቸውን ኮርሶች ማፀደቅ

5) የተከታታይ የሙ.ያ ማጎልበቻ ኮርሶችን የሚሰጡና ለኮርሶቹ እውቅና የሚሰጡ ድርጅቶች ሊከተሉአቸው ወይም ሊያሟሉ የሚገባቸውን ደረጃዎች ማዘጋጀትና መፈፀማቸውን ማረጋገጥ

6) የተከታታይ የሙ.ያ ማጎልበቻ ኮርሶችን እውቅና በሚሰጡ ድርጅቶች ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን መገምገምና እንደአስፈላጊነቱ እርምጃ መውሰድ

7) ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከክልል ጤና ቢሮዎችና ከሙ.ያ ማህበራት ጋር በመሆን በየአመቱ ተከታታይ የሙ.ያ ማጎልበቻ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ እና ተግባሮቹን መለየት

8) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተከታታይ የሙ.ያ ማጎልበቻ እውቅና ለመስጠት የሚረዱ ማኑዋሎችን መከለስ

## 10. የኮሚቴዎች የስብሰባ ጊዜ

1) የጤና ሙ.ያ የስነ-ምግባር ኮሚቴ በወር አንድ ጊዜ በመደበኛነት ይሰበስባል፡፡ እንደ አስፈላጊነቱ ንዑሳን ኮሚቴዎችን ጨምሮ በየጊዜው ይሰበሰባሉ፤

2) ብሄራዊ የጸረ ተህዋሳያን መድሃኒቶች አማካሪ ኮሚቴ በየሩብ አመቱ አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፡፡ አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥም እንደአስፈላጊነቱ ሊሰበሰብ ይችላል፤

3) የትምባሆ ቁጥጥር ትግባር አሰተባባሪ ኮሚቴ፣ ብሄራዊ የመድኃኒት አማካሪ ኮሚቴ እና የጤና ባለሙ.ያዎች የተከታታይ የሙ.ያ ማጎልበቻ ኮሚቴ በወር አንድ ጊዜ በመደበኛነት ይሰበሰባሉ፡፡ እንደ አስፈላጊነቱ አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥም ሊሰበሰቡ ይችላሉ፡፡

# ክፍል ሦስት

# የኮሚቴ አባላት ክፍያ አተገባበር፤ ጊዜና መጠን

## *11. የኮሚቴ አባላት ክፍያ*

የኮሚቴ አባላት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 መሠረት ክፍያቸው የሚፈጸም ይሆናል፡፡

1) ለኮሚቴ አባላት ክፍያ ሊከፈል የሚችለው በስብሰባ ሲገኙና መገኘታቸውንም የሚያረጋግጥ የስም ዝርዝር የያዘ ፎርማ እና የሰዓት መቆጣጠሪያ ሰነድ በሚመለከተው አስተባባሪ ዳይሬክቶሬት ተረጋግጦ ለፋይናንስና አቅርቦት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት በደብዳቤ ሲቀረብ ይሆናል፡፡

2) የባለስልጣን መ/ቤቱ ሰራተኛ የኮሚቴ አባል ወይም ፀሀፊ ሆኖ ስራውን ሲሰራ ክፍያው የሚመለከተው ሆኖ በአንቀፅ 13 በሰንጠረዥ በተቀመጠው መጠን መሰረት ክፍያ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መስረት ተረጋግጦ በቀረበው መሰረት ክፍያ የሚፈጸመው ስብሰባው ከተካሄደበት ቀን በኋላ በሚደረግ ስብሰባ ይሆናል፡፡

## *12. የክፍያ መግለጫ*

1) የአበል ክፍያ ታሳቢ የሚያደርገው የኮሚቴው ሰብሰቢና አባላት በስብሰባ ተገኝተው ለሰጡት የቴክኒክ ምክር ሊያገኙት የሚገባ ገቢ ወይም የትራንስፖርትና ሌሎች ወጪዎችን ታሳቢ በማድረግ ይሆናል፡፡

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የክፍያ አፈፃፀሙን በተመለከተ የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በዚህ መመሪያ በተጠቀሱት እና በተመሳሳይ አላማ የሚቋቋሙት ኮሚቴዎች የስራ ኃላፊነት፣ ወቅታዊ አስፈላጊነት፣ ጊዜ፣ ጉልበት እና ሌሎች ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ የክፍያ መጠኑን ሊወስን፣ ሊቀይር፣ ሊያሻሽል ፣ሊሽር ወይም ሌሎች አስፈላጊ የሚላቸውን ሁኔታዎች ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 13. የኮሚቴ አባላት ክፍያ መጠን

የክፍያ መጠን ሰንጠረዥ

| ተ ራ. ቁ | የኮሚቴ ስም | የክፊያ መጠን በብር | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አዲስ አበባ በቀን | | ከአዲስ አበባ ውጪ በቀን | |
| | | ሰብሳቢ | አባል | ሰብሳቢ | አባል |
| 1 | የጤና ሙያ የስነ-ምግባር ኮሚቴ | 600 | 500 | 400 | 400 |
| 2 | ብሄራዊ የመድሃኒት አማካሪ ኮሚቴ፣ | 500 | 400 | 300 | 300 |
| 3 | ብሄራዊ የጸረ ተህዋሳያን መድሃኒቶች አማካሪ ኮሚቴ፣ | 500 | 400 | 300 | 300 |
| 4 | የትምባሆ ቁጥጥር ትግባራ አሰተባባሪ ኮሚቴዎች | 400 | 300 | 200 | 200 |
| 5 | የጤና ባለሙያዎች የተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ኮሚቴ | 500 | 400 | 300 | 300 |

## 14. ተፈፃሚነት የሌላቸው ህጎች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 15. የተሻረ ህግ

በባለስልጣኑ ስር ለሚገኙ የቴክኒክ ኮሚቴዎች የአበል ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 29/2007 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

## 16. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ህዳር 17/2009 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

የሁሉ ደነቀው

የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን

ዋና ዳይሬክተር